# <u>ስደተኞችና ጥገኞች፡- ስለ ቅጽ 1-9 ምን ለማወቅ ይፈልጋሉ</u>

ዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካ ውስጥ ስራ ለመስራት የስራ ፈቃድ እንዳለዎት ለማረጋገጥ የሚያገለግለውን የመንግስት ቅጽ የሆነውን "ቅጽ I-9" መሙላት አለብዎት። ***ሕጉን ተግባራዊ የማያደርጉ አሰሪዎች <u>በእርስዎ ላይ መድሎ ሊፈጽሙ ይችላሉ።</u>***

## *ለቅጽ 1-9 ክፍል 1 እርስዎን የሚመለከቱ መረጃዎችን ማቅረብ አለብዎት።*

- ስደተኞችና ጥገኞች "የስራ ፈቃድ የተሰጣቸው የውጭ ሃገር ሰዎች" እንደሆኑ ይታሰባሉ። ስራ ለመስራት የሚያስችል ቋሚ መብት ስላለዎት የተሰጠዎት የስራ ፈቃድ የአገልግሎት ዘመን የሚያበቃበት ቀን በሚለው ቦታ ላይ "N/A" ("Not Applicable") ማለትም ("አግባብነት የለውም") ብለው መጻፍ አለብዎት።
- ለማቅረብ የፈለጉት የስደተኝነት ምዝገባ ቁጥርን ሳይሆን I-94 የመግቢያ ቁጥርን ከሆነ፤ ፓስፖርት ካለዎት በፓስፖርትዎ ላይ ያሉትን መረጃዎች ያቅርቡ። ፓስፖርት ከሌለዎት የፓስፖርት መረጃዎች የሚለው ቦታ ላይ "N/A" ማለትም አግባብነት የለውም ብለው መጻፍ አለብዎት።
- የእርስዎ I-94 ካርድ ሰረዝ የተደረገበት ቁጥር ጋር በእጅ ጽሑፍ የተጻፈ ቁጥር ያለው ሲሆን በእጅ ጽሑፍ የተጻፈው ቁጥር የእርስዎ I-94 ቁጥር ነው።

## *ለቅጽ 1-9 ክፍል 2 ማንነትዎንና የስራ ፈቃድ እንዳለዎት የሚገልጹ ሰነዶችን ለቀጣሪዎ ማቅረብ አለብዎት።*

- ቅጽ I-9 ተቀባይነት ያላቸው ሰነዶች ሶስት ዝርዝር አለው። እነዚህ ዝርዝሮችም – ዝርዝር ሀ (ማንነትንና የስራ ፈቃድን በጣምራ የሚገልጹ ሰነዶች)፣ ለ (ማንነትን የሚገልጹ ሰነዶች) እና ሐ (የስራ ፈቃድን የሚገልጹ ሰነዶች) ናቸው። ከዝርዝር ሀ <u>አንዱን</u> ሰነድ <u>ወይም</u> ከዝርዝር ለ አንድ እና ከዝርዝር ሐ አንድ ሰነድ በማጣመር ምርጫዎን ማሳየት ወይም ማሳወቅ አለብዎት።
- በስቴት የተሰጠዎት የመታወቂያ ካርድና ገደብ አልባ የማኅበራዊ ደሕንነት ካርድ ካለዎት ቀጣሪዎ የስራ ፈቃድ ሰነድ እንዲያሳዩ መጠየቅ አይችልም።
- ስደተኛ ከሆኑ፤ የእርስዎ I-94 ስራ ከተቀጠሩበት ቀን ጀምሮ ለ90 ቀናት ያክል የሚያገለግል የዝርዝር ሰነድ ነው። ከ90 ቀናት በኋላ ከዝርዝር ሀ ሌላ ሰነድ ወይም ከዝርዝር ለ አንድ ሰነድና ከዝርዝር ሐ አንድ ሰነድን በማጣመር ማሳየት አለብዎት።
- ጥገኝነት ጠያቂ ከሆኑ፤ I-94 ሰነድዎን በዝርዝር ሐ ውስጥ እንደተጠቀሰ ሰነድ መጠቀም ይችላሉ።

## *ቀጣሪ ሰነዶችን ድጋሚ መጠየቅ የሚችለው በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ ብቻ ነው።*

- ለክፍል 2 የስራ ፈቃድ ሰነድዎን ካሳዩ የስራ ፈቃድ ሰነድዎ የሚያገለግልበት ጊዜ ሲጠናቀቅ አሰሪዎ ሌላ ሰነድ እንዲያሳዩ ሊጠይቅዎት ይችላል። ይህ ጥያቄ ሲቀርብልዎት የአገልግሎት ዘመኑ ያላበቃ አንድ ሰነድ ከዝርዝር ሀ <u>ወይም</u> ከዝርዝር ሐ መካከል ለምሳሌ ገደብ አልባ የማኅበራዊ ደሕንነት ካርድ እንደ ምርጫዎ <u>አንዱን</u> ሰነድ ሊያሳዩ ይችላሉ። የስራ ፈቃድ ሰነድን በድጋሚ ማሳት የለብዎትም።
- ለክፍል 2 ዝርዝር ለ እና ዝርዝር ሐ ውስጥ የተጠቀሱ ለምሳሌ የስቴት የመታወቂያ ካርድ እና ገደብ አልባ የማኅበራዊ ደሕንነት ካርድ የመሳሰሉ ሰነዶችን ካሳዩ የስራ ፈቃድ ሰነድዎ የአገልግሎት ጊዜ ቢጠናቀቅም እንኳ ቀጣሪዎ ሰነዶችዎን እንዲያሳዩ በድጋሚ መጠየቅ <u>የለበትም</u> ወይም መጠየቅ አይችልም።

## *ስራ ለመጀመር የማኅበራዊ ደሕንነት ቁጥርዎን የማቅረብ ግዴታ የለብዎትም።*

- ቀጣሪዎ በወቅቱ የማኅበራዊ ደሕንነት ቁጥር ባይኖርዎትም እንኳ ስራ እንዲሰሩ መፍቀድና ለስራዎ ክፍያ መፈጸም <u>አለበት</u>።
- ስራ መስራት በጀመሩበት ወቅት ቁጥርዎን ካልያዙ ክፍል 1 ውስጥ የሚገኘውን የማኅበራዊ ደሕንነት ቁጥር ሳጥንን እንዳለ ክፍት ይተዉት። አሰሪዎ የቅጥር ማረጋገጫ (E-Verify) የሚጠቀም ቢሆንም እንኳ ይህ ሁኔታ ይሰራል።

**ስለ ቅጽ 1-9 እና መድሎ ተጨማሪ ጥያቄ ካለዎት ከክፍያ ነጻ በሆነው ስልክ ቁጥራችን 1-800-255-7688 ይደውሉልን ወይም የድረ-ገጽ አድራሻችን <u>www.justice.gov/crt/about/osc</u> ላይ ይጎብኙን። የውጭ ቋንቋ አስተርጓሚዎች አሉን።**